# ልጁን የሚበላ

አዴፓ ተብሎ ፣ የተጫነው ባገር
ጠፍጥፋ የሰራችው ፣ ያቺ ያገር መዥገር
መች አማራ ሆነ ፣ አባይን ቢሻገር
ያሸብራል እንጂ ፣ አገርና መንደር ።

ኢህዴን አዴፓ ፣ ስሙን ቢቀይርም
ፈጣሪው ወያኔ ፣ ከዐይን ቢሰወርም
እሱ የተሰራበት ፣ በምስል በግብርም
ለመጣው ማጎብደድ ፣ ሎሌነቱ አይቀርም ።

ጥርሱን የነቀለው ፣ ወገን እያስፈጀ
ባጎብድዶ መኖር ፣ ያረጀ ያፈጀ
እንኳን ለወገኑ ፣ ለራሱም ያልበጀ ፣
በሎሌነት ተግባር ፣ ዛሬም እንደ ጥንቱ
ለጠላቱ ሳይሆን ፣ ወገን ላይ ጉልበቱ
የአማራን ወጣት ፣ አሳደው ሲመቱ
ኑሮው ባሽከርነት ፣ ክህደት ሃይማኖቱ ።

አይናችን እያየ ፣ ጆሮም እየሰማ
አማራው በጅምላ ፣ መብቱ እየተቀማ
በሰለጠነ አሽከር ፣ ወገን እየደማ
አዴፓ የሚባል ፣ ተሸክሞ አሳማ
ትግል አይሳካም ፣ ጆሮ ያለው ይስማ ።

ውሉ ያልታወቀ ፣ ድመት ይሁን ሌላ
ከኛም ከነሱም ጋር ፣ ተክሎ ሁለት ባላ
ህዝብ እየጎተተ ፣ ሁሌም ወደኋላ
አዛኝ አንዳች መሳይ ፣ ለአማራው ያደላ
አይጦቹን ትቶ ፣ ልጁን የሚበላ
አማራ ነኝ ይላል ፣ የሰው ደም ሲያፈላ
ከህዝቡ ጫንቃ ላይ ፣ መች ነው የሚከላ ።

ታዛቢው

August 7, 2019